# ከጅብ ጅማት የተሠራ ክራር ቅኝቱ እንብላው እንብላው ብቻ ነው።

(ባይሳ ዋቅ-ወያ)

ሻለቃ ዳዊት፣ የእግዚአብሔር ሰላምታዬን አስቀድማለሁ፣ ማርች 14, እና አፕሪል 8, 2019 ዓ/ም በተለያዩ መጽሄቶች ላይ በእንግሊዝኛ ያሳተሟቸውን ሁለት ተከታትይ መጣጥፎችዎን በጥሞና አነበብኳቸው። የብሄሮች እርስ በርስ ግጭትና ያስከተከሉት መፈናቀል፣ መንግሥት የሚራምደውን የማፈናቀልና "ዘር የማጥራት ፖሊሲ" የዶ/ር ዓቢይ በዘር ፖሊቲካ ተጽዕኖ ሥር መውደቅና አገሪቷን ለመታደግ ብቃት እንደሌለው፣ ጃዋርና OMN አገሪቷን ለዘር ማጥፋት ወንጀል (Genocide) እያዘጋጁ መሆናቸውንና ሌላ ሌላም ተጓዳኝ አገራዊ ችግሮችና ሥጋትዎን አስረድተውናል። የሁለቱም ጽሁፍዎ ይዘት ተመሳሳይ ስለሆነ ባንድ ላይ በመጭመቅ፣ ስላነሷቸው ነጥቦች ያለኝን ሃሳብ እንደሚከተለው ለማስቀመጥ ወሰንኩ።

ሻለቃ ዳዊት! እንደስዎ አባባል፣ የኢህአዴግ መንግሥት ላለፈው ሃያ ሰባት ዓመት "ህዝብን በማፈናቀልና በማስፈር ብቻ ሳይወሰን "ብሄርን በማጥራት" *(ethnic cleansing)* ላይ ያተኮረም ነበር። በኔ ግምት ኝ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደ አገራዊ ፖሊሲ ህዝብን ማፈናቀል የጀመረው በስዎ የሥልጣን ዘመን ማለትም በደርግ አገዛዝ ዘመን ነበር። የወሎና የትግራይ ወገኖቻችንን ከቤታቸው በግድ አፈናቅሎ ወለጋና ባሌ አካባቢ ያሰፈራቸውና አፈጻጸሙን በተመለከተ እስዎ በግንባር ቀደምትነትና ዋና ተዋናይነት የተካፈሉበት የደርግ መንግሥት ነበር። ህዝብን የማፈናቀል ታሪክ የተጀመረው እስዎ እንደሚሉት በዛሬው የኢትዮጵያ መንግሥት ሳይሆን በስዎ መንግሥት ነበር ለማለት ነው። እኔም እንደስዎ ኑሮዬ ከባህር ማዶ ስለሆነ የኢህአዴግ መንግሥት በኢንቬስትመንት ሰበብ "ህዝብን እንዳፈናቀለና አልፎ አልፎም እንዳሰፈረ" ባውቅም፣ "ብሄርን የማጥራት" ፖሊሲ ነበረው ብዬ ለማመን ግን ያዳግተኛል። እስዎ የዘረዘሯቸው የኢህአዴግ የሰብዓዊ መብት መጣሱ ዕውነት ሆኖ እያለ "ብሄርን ማጥራት" የሚያክል ዓለም አቀፋዊ ወንጀል መፈጸሙን ግን እርግጠኛ አይደለሁም። እስዎም ያለዎትን ተጨባጭ ማስረጃዎችዎን ቢያቀርቡ ኖሮ ተዓማኒነትዎን ከፍ ያደርግ ነበር። ግን አላቀረቡም።

የክልል መንግሥታት "ብሄርን የማጥራት" ወንጀል እንደሚፈጽሙ ከዚህም በፊት አንዳንድ ጸሃፊዎች ዳር ዳር ይሉ የነበረው "የክልል መንግሥታትና ህዝቦች ከክልላቸው ብሄር ውጭ ሌላው የኢትዮጵያ ብሄር ተወላጅ እንዲኖር አይፈልጉም፣ ይህንንም ያመጣው የኢትዮጵያ በክልሎች መከፋፈል ነው" ይሉ የነበረውን እርስዎም ይህንኑን በጹፍዎ በተዘዋዋሪ መንገድ አንጸባርቀዋል። አዎ! በተለያየ ጊዜና በተለያዩ ክልሎች የአንድ ብሄር ህዝብ ከሌሎች የክልሉ ብሄር ህዝቦች ጋር እየተጋጩ ነበር። "የሌላ ብሄር ተወላጅ" በመሆናቸው ብቻ የመፈናቀል አደጋ የተነጣጠረባቸውም ነበሩ። ዛሬም እየተነጣጠረባቸው ነው። ከጉሙዝ ክልል ቁጥራቸው በርከት ያለ የአማራና የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች በአማራነታቸውና በኦሮሞነታቸው ብቻ ተነጥለው ለመፈናቀል አደጋ ተዳርገዋል። ከሱማሌ ክልልም እንደዚሁ ከሚሊዮን በላይ የሆኑ የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች በኦሮሞነታቸው ብቻ ተለይተው እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል። በቅርቡም እንደሰማነው ከሆነ ቁጥራቸው ብዙ የሆነ የቅማንትና የአገው ህዝብ በብሄር ማንነታቸው ብቻ ለመፈናቀል ተዳርገዋል የሚል ዜና እየተሰማ ነው። የክስተቶቹ ዕውኔታነት እንዳለ ሆኖ ግን፣ የማፈናቀል ድርጊቱና፣ አልተከሰተም እንጂ ተከስቷል የሚሉትም "የብሄር ማጥራት" ወንጀል የተቀነባበረው በመንግሥት ነው የሚለውን ግን ለመቀበል ይከብዳል።

በተለያዩ ያገራችን ክፍሎች በብሄሮች መካከል የተነሳው ግጭት "ብሄርን ለማጥራት" እንዳልሆነ የሚያሳየው፣ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የአማር ብሄር ተወላጆች እንኳን ከቄያቸው መፈናቀል ይቅርና አንዳችም "የባዕድነት ስሜት" ሳይሰማቸው ለዘመናት በኖሩበት አካባቢ ከጎረቤቶቻቸው ጋር እዚያው ኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሰላም እየኖሩ ነው። ብዙዎቹም የክልሉን የመሥርያ ቋንቋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የክልሉ ሕገ መንግሥት በደነገገው መሠረት ከኦሮሞዎች እኩል በመንግሥት ሥራ ተመድበው ወይም ተመርጠው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ከጉሙዝ ክልል በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች በግፍ የተፈናቀሉትን ያህል እዚያው በክልሉ ዋና ከተማ በአሶሶ ደግሞ ከሲሶ በላይ የሚሆነው ነዋሪና በክልሉ መንግሥት አስተዳደርም ውስጥ የዚያኑ ያህል ቁጥር ያላቸው ኦሮሞዎች ካለመፈናቀላቸውም በላይ፣ ተመድበው ወይም ተመርጠው በተለያዩ የክልሉ መንግሥት መሥርያ ቤት ውስጥ በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ስለዚህ እኔ እስከማውቀው ድረስ የራሱን ክልል ከሌላው ብሄር ወይም ብሄሮች ለማጥራት ብሎ አንድን ብሄር ነጥሎ ያገለለ ወይም ያፈናቀለ ክልል የለም ማለቴ ነው። ስለዚህ ነው "በክልል ባለቤትነት" ዙርያ በኢትዮጵያ ብሄሮች መካከል ግጭት አለ የሚባለውን ትርክት ለመቀበል በጣም የሚያዳግተኝ። ምክንያቱም፣

***በመጀመርያ ደረጃ፣*** <u>በየትም ዓለም በህዝቦች መካከል ግጭትን የሚያስከትል ተፈጥሮያዊ አለመግባባት ኖሮ አያውቅም።</u> በጥቃቅን የአስተዳደግና የአኗኗር ዘይቤ ይለያይ እንደው እንጂ፣ የሰው ልጅ በየትም ዓለም ቢሆን ሲፈጠር ጀምሮ አንድ ዓይነት ተፈጥሮያዊ የሆነ <u>የደግነት</u> ባህርይ አለው። ለዚህም ነው የግለሰብ እንጂ የህዝብ ክፉ ወይም መጥፎ የለም የሚባለው። ለዚህም ነው "ያንድ ክልል ህዝብ" "የሌላውን ብሄር ህዝብ" በጥላቻ ተነሳስቶ ያፈናቅላል ብዬ ለማመን የሚከብደኝ። ባለፉት 30

ዓመታት በተለያዩ የዓለም ክፍላት ተዘዋውሬ የግጭቶች ሰለባ ከሆኑ ህዝቦች ጋር ስሠራ አንድ የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር፣ ሌላ የውጪ ኃይል ካላነሳሳቸውና ካልገፋፋቸው በስተቀር፣ የትም አገር አንድ ህዝብ በሌላው ላይ በጥላቻ ተነሳስቶ ሲያጠቃ አላየሁም። ያ ገፋፊ ወይም አነሳሳሽ ኃይል ደግሞ፣ ለምሳሌ አገራችንን ኢትዮጵያን የወሰድን እንደሆነ፣ እንደ እኔና እንደ እስዎ ያለን ተምረናል የምንል ባብዛኛው ከውጭ ሆነን ግጭቶችን የምናባብስ ኢትዮጵያዊያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነን።

***በሁለተኛ ደረጃ፣*** ስለ ህዝቦች መፈናቀል በተነሳ ቁጥር፣ በግልጽም ሆነ እስዎም በተዘዋዋሪ ለማለት እንደሞከሩት፣ የችግሩ መንሥዔ ያገሪቷ በፌዴራሊዝም ሥርዓት መሠረት በክልሎች መከፋፈሏን አድርጎ መቁጠርና፣ ስለሆነም የፌዴራል ሥርዓቱና በተለይም ክልላዊ አስተዳደሩ ካልጠፋ ችግሩ አይፈታም የሚል ሙግት ከተለያየ አቅጣጫ እየተሰማ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወደፊት በሚያደርገው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚፈልገውን የአስተዳደር ሥርዓት የመምረጥ መብት ስላለው ፌዴራላዊ ሥርዓቱንና ክልላዊ አስተዳደሩን የመቀየር ፍጹማዊ መብት እንዳለው እንደታወቀ ሆኖ፣ ዛሬ በምንተዳደርበት ፌዴራላዊ ሕገ መንግሥትም ሆነ የዘጠኙ ክልሎችም ሕገ መንግሥት ግን <u>“ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የኢትዮጵያ ግዛት (ክልል) በነጻ የመዘዋወርና የመኖር፣ የክልሉን የመሥርያ ቋንቋ እሳካወቀ ድረስ ደግሞ በማንኛውም የክልሉ መንግሥታዊ ተቋም ተመድቦ ወይም ተመርጦ ሊሰራ ይችላል”</u> ብለው ስለደነገጉ፣ ክልሎች ታጥረው ራሳቸውን “ከሌላው ክልል ብሄር ለመከላከል” ዝግ ኬላ እንዳጠሩ አድርጎ ማቅረብ ቅንነት የጎደለው አካሄድ ይመስለኛል።

ሌላው ያነሱት ነጥብ “ስለ ጃዋር እና ጃዋር በዳይሬክተርነት ስለሚመራው OMN ስለሚባለው የሳቴላይት ቴሌቪዥን ጣቢያ ነው። በስዎ አባባል የድርጅቱ ዳይሬክቴርም ሆነ ድርጅቱ ራሱ “የጥላቻ ንግግርንና ጽንፈኝነትን” እንዲያስፋፉ መንግሥት ድጋፍ የሰጣቸው እንደሆነና፣ በግለሰቡም ሆነ በድርጅቱ ላይ አስቸኳይ እርምጃ ካልተወሰደ ባገሪቷ ላይ የሩዋንዳ ዓይነት የዘር ማጥፋት ወንጀል (Genocide) ሊከሰት ይችላል የሚለው ነው። የዘር ማጥፋት ወንጀል በመሰረቱ፣ የሆነ የሰው ልጅ ዘርን ከሌሎች ለይቶ ለማጥፋት በተግባር የሚውል የተቀነባበረ የወንጀል ሥራ ስለሆነ፣ በዛሬው ሁኔታ ይህንን አሰቃቂ ወንጀል ለመፈጸም እየተዘጋጀ ያለው የኢትዮጵያ ብሄርና የወንጀሉም ዒላማ የሚሆነው ብሄር የትኛው እንደሆነ ሳይነግሩን እንደው በደፈናው “እመኑኝ” እውነቴን ነው የምላችሁ “የዘር ማጥፋት ወንጀል” በ OMN እየተተለመ ነው ይሉናል። እንደ አንድ ዜጋ ሥጋትዎን መግለጽዎ አግባብ ሆኖ እያለ፣ እንደው ዝም ብሎ ያላንዳች አስተማማኝ ማስረጃ ግለሰብንም ሆነ ድርጅትን መወንጀል ግን ካንድ የሕግ ባላሙያ ነኝ ከሚል ግለሰብ የሚጠበቅ አይደለም። ምናልባት እስዎ የለመዱት ያኔ በደርግ ዘመን በጥርጣሬ ብቻና ያላንዳች ሕጋዊ ማስረጃ ያንድን ትውልድ ምርጥ ዘር በቀይ ሽብር፣ የፊውዳል ርዝራዥ ወይም ቀይ መንገደኛ እያላችሁ ዜጎችን በጅምላ መግደላችሁ ትዝ ብሎዎት ከሆነ፣ እባክዎን ከዕንቅልፍዎ ይባንኑ። ያ በታሪካችን ውስጥ ጥቁር ነጥብ ጥሎ አልፏል። ዛሬ ያለው መንግሥት “መርምረን እናስራለን እንጂ አስረን አንመረምርም” የሚል ስለሆነ፣ ግለሰቡም እንዲታሰርና ድርጅቱም እንዲዘጋ ከፈለጉ ያለዎትን መረጃና ማስረጃ በይፋ ቢያቀርቡ፣ ሁላችንም ከጎንዎ ተሰልፈን መንግሥት በሁለቱም ላይ ባስቸኳይ እርምጃ ወስዶ አገራችንን፣ እስዎ በዓይኔ አያቻለሁ ስለሚሉትና ብዙዎቻችን ግን በቴሌቪዥን መስኮቶቻችን ብቻ ካየነው የሩዋንዳ ዓይነት የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲታደገን በሰልፍ እንወጣ ነበር።

በዓለም አቀፍ ሕግ፣ “የዘር ማጥፋት ወንጀል” በግለ ሰብ ሳይሆን በአንድ በተደራጀ ቡድን ወይም የፖሊቲካ ሥልጣን ባለው ኃይል የሚተገበር፣ የወንጀሎች ሁሉ ወንጀል ነው። በኔ ግምት የርስ በርስ ጦርነትና “የዘር ማጥፋት ወንጀል” የተማታብዎት ይመስለኛል። አዎ! አገራችን ውስጥ የርስ በርስ ጦርነት ሊከሰት እንደሚችል ብዙ ምልክቶች ይታያሉ። እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ሰማንያ ስድስት ብሄርና ቋንቋ እንዲሁም የተለያዩ ኃይማኖቶችን የምታስተናግድ ደሃ አገር ይቅርና፣ እንደ ሱማሌ ሊቢያና የመንን የመሳሰሉ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ፣ ከሞላ ጎደል አንድ ኃይማኖት የሚከተሉ ሕዝቦችም ከርስ በርስ ጦርነት ስላልዳኑ፣ ሥጋታችን አግባብነት አለው። እርስዎን ያስፈራዎት ግን የርስ በርሱ ጦርነት ሳይሆን፣ OMN በተባለው “ጽንፈኛ” ጣቢያ አማካይነት በሚሠራጨው “የዘር ማጥፋት ወንጀል” ቅስቀሳ መሠረት የሆነ “ግምታዊ” ብሄር በሆነ “ግምታዊ” ብሄር ላይ ተነሳስቶ <u>የዘር ማጥፋት ወንጀል</u> ይፈጽማል የሚለው ግምታዊ “ሥጋት” ነው። በኔ ግምት ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ማለትም የሌለን እንቅስቃሴ እንዳለ አቅርቦ፣ አንድ ብሄር በሌላው ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊፈጽም እየተዘጋጀ ነው ብሎ መቀስቀስ ራሱ ወንጀል ነው ብሎ ሌላ ተቆርቋሪ ዜጋ ሊከስዎት ይችላልና ቢያስቡበት መልካም ይመስለኛል። በተረፈ ግን፣ OMN የግለሰብ ንብረት ሳይሆን በተለያዩ መስኮች ዝናን ባተረፉ የምሁራን ቦርድ የሚመራ የኦሮሞ ሕዝብ አንጡራ ሃብትና የመላው የኦሮሞ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ሆኖ እያገለገለ ያለ ጣቢያ ስለሆነ ይህንን ሕዝባዊ ጣቢያ ይዘጋ፣ ወይም ፈቃዱን ይነጠቅ ብለው ሲለፍፉ፣ ጥላቻዎ ከዳይሬክተሩ ከጃዋር ጋር ሳይሆን ከመላው የኦሮሞ ሕዝብ ጋር እንደሆነ ቢረዱት ይበጃል ባይ ነኝ።

ጃዋርን በተመለከተ፣ ራሱን ለመከላከል እንኳን “አንድ ሻለቃ” ጦር ይቅርና አንድ ባታሊዮንን ሊመክት የሚያስችለው ሰብዓዊ ክህሎት አለው ብዬ ስለምገምት፣ “እሱን ለሱ” ልተወው። እኔን ያሳሰበኝ የስዎ፣ OMNን በቱትሲዎች ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲፈጸም ሲሰብክ ከነበረውና በጽንፈኛ ሁቱዎች ይተዳደር በነበረው የሩዋንዳው RTLM ጋር ማመዛዘንዎ ነው። ይህ አባባልዎ፣ አንድም የ OMNን ታሪካዊ አመጣጥ በውል ካለማወቅ አለያም ደግሞ፣ “አንድ ግምታዊ ብሄርን ከዘር ማጥፋት

ወንጀል ለማዳን” በሚል ሰበብ ድርጅቱ እንዲዘጋ መትጋትዎ፣ ሆን ብለው በጣቢያው ተጠቃሚ አርባ ሚሊዮን ኦሮሞ ሕዝብ ላይ ያለዎትን ጥላቻ በእጅ አዙር ለመግለጽ የፈለጉ መሰለኝ። ይህ እጅግ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። የፈለጉትን ለመውደድ ያልፈለጉትን ደግሞለየመጥላት መብትዎ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ብዙ የግል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ውስጥ OMNን ብቻ ያላንዳች አሳማኝ ማስረጃ ነጥለው ለመምታት ማነጣጠጥርዎ ግን አነሰ ቢባል ቅንነት የጎደለው አካሄድ ይመስለኛል። ግን ለምን ያን ሁሉ መንገድ መጓዝ አስፈለገዎት?

የኦሮሞ ሕዝብ ዘመናዊዋ ኢትዮጵያ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በታሪኩ ለመጀመርያ ጊዜ በብሄራዊ የሬዲዮ ጣቢያ በቋንቋው የተላለፈው ፕሮግራም ደርግ ሥልጣን በወሰደ ሰሞን ነበር። አዎ! ያ የሰላሳ ደቂቃ የኦሮሚኛ ፕሮግራም ያኔ በትምህርት ቤት እንዳንማረውና በየመንግሥት መሥርያ ቤትም እንዳንገለግለበት የተከለከልነውን ቋንቋችንን በብሄራዊ ሬዲዮ ስንሰማው ለብዙዎቻችን ዘጠነኛው ደመና የገባን ያህል ነበር ይመስጠን የነበረው። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳየው ግን፣ ያኔ በዚያች ሰላሳ ደቂቃ ውስጥ ያገር ውስጥና የውጭ አገር ዜና ተሰምቶ፣ የፍየል ወጠጤ ተዘፍኖበት፣ የተገደሉት ወይም የተያዙት ባላባቶች ስም ዝርዝር ተነግሮበት፣ ለአንድ ወይም ሁለት የኦሮሚኛ ዘፈን የሚበቃ ጊዜ መኖሩ በጣም ያስገርመኛል። ታዲያ ከዚያ የአንድን ብሄር ቋንቋ ከፍ አድርጎ የሌሎቹን ከሚያሳንስ ወይም ሌላ ቋንቋ እንዲነገር ከማይፈቅድ ሥርዓት ተነስተን ዛሬ በኦሮሚኛ ቋንቋ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀኑን ሙሉ ወደሚያስተላልፍ ዘመን ስንሻገር፣ ለኛ ለኦሮሞዎች የሚሰጠን ልባዊ ደስታ ለስዎ ዓይነቱ የዚያኛው “ሥርዓት ናፋቂዎች” ግን ለምን እንደማይመቻችሁ ሁሌም አልገባ ያለኝ ነገር ነው። አልገባ ብሎዎት ነው እንጂ OMN፣ መላው የኦሮሞ ሕዝብ በዘመናት ትግሉ ውስጥ ውድ ዋጋ ከፍሎበት ያመጣውና የትግሉ ፍሬ ከመሆኑም በላይ፣ ጣቢያው የኦሮሞን ሕዝብ ባሕልና ሥነ ጽሁፍ ለማሳደግ፣ ማህበረሰባዊ ኤኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እንጂ የማንንም የኢትዮጵያን ብሄር ህገ መንግሥታዊም ሆነ ሰብዓዊ መብት የማይጥስ ስለሆነ፣ ከስዎ ጎራ ስለሚነዛው በጭፍን ጥላቻ ላይ ለተመሠረተ ክስ መስሚያ ጆሮም የለንም። አትረፍ ያለው በሬ ቆዳው ለከበሮ ይውላል እንዲሉ፣ እስዎም ዕድሜ ልክዎን የኖሩት ያንድን ብሄር የበላይነት የሚያራምደው ሥርዓት በብሄሮች እኩልነት ሥርዓት መለወጡ ያልተመቸዎት ስለሆነ ዕድሜ ልክዎን ሲለፉ ይኖሯታል እንጂ የኦሮሞ ሕዝብ ካሁን በኋላ ወደዚያ የጨለማ ሕይወት አይመለስም። OMNም የማንንም ብሄር መብት ሳይነካ፣ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመላው የኦሮሞን ሕዝብ የማያወላውል ድጋፍ ተንተርሶ መትጋቱን ይቀጥልበታል።

ስለ “ዘር ማጥፋት ወንጀል” ካነሱ አይቀር ዘንዳ፣ እስዎ ያላንዳች ምክንያት OMNን ከሩዋንዳው RTLM ጋር ያመሳሰሉበት የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ማስረጃ እንደሌለዎት በርግጠኝነት ለመናገር እችላለሁ። የOMNን ፕሮግራሞች መከታተል ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ አንድም ቀን፣ እደግመዋለሁ፣ አንድም ቀን አንድም ፕሮግራሙ ያንድን ሕዝብ መብት ሲጥስ ወይም አንድን ብሄር ለማሳነስ ሲውል አላስተዋልኩም። ምናልባት ኦሮሚኛ ቋንቋ አለመቻልዎና እንደ አብዛኛው ጓደኞችዎ ለግምትዎ ቅርጽ ያበጁት በወሬ ወሬ ላይ ተመርኩዘው ከሆነ፣ በቀረችው የዕድሜ ዘመንዎ ኦሮሚኛን ቢማሩት፣ በተሳሳተ ወይም የተጣመመ ትርጉምን እንደ ዋቢ ይዞ ይህን መሰል መሠረት ቢስ ክስ አቅርበው ራስዎን ከማስገመት ይድኑ ይሆናልና ያስቡበት ባይ ነኝ።

ውድ ሻለቃ! የህትመት፣ የድምጽና የቪዲዎ ፕሮግራሞች የሚያስተላፏቸው መልዕክቶች ልክ እንደ ኑክሌር ኃይል የመግደልም የማዳንም ባህርይ አሏቸው። ወሳኙን ሚና የሚጫወተው መልዕክት አስተላላፊው ነው፤ በዚህ መልኩ ከታየ፣ የሚያጠያይቀው ቅንነትዎ ነው እንጂ የሚዲያን አሉታዊ ሚና አንስተው ስጋትዎን መግለጥዎ አግባብነት አለው። በኔ ግምት OMN ያንን አሉታዊ ሚና አይጫወትም ባይ ነኝ እንጂ፣ ሌሎች የግል የሚዲያ ተቋማት እስዎን ያሳሰበውን ህዝቡን ወደርስ በርስ ግጭት ሊመራ የሚችል አሉታዊ ፕሮግራም በተደጋጋሚ ያቀረቡ እንዳሉ አምናለሁ። በዚህ ደረጃ ከሚፈረጁት ተቋማት ለምሳሌ አንዱ ESAT ነው። እኔ ከስዎ በተሻለ ሁኔታ ESATን በዘር ማጥፋት ወንጀል እንኳ ባይሆን በሕዝቦች መካከል ጥላቻን በማስፈን ከ RTLM ያላነሰ ሚና እየተጫወተ መሆኑን በመረጃና ማስረጃ የተደገፈ ክስ ለማቅረብ እችላለሁ። ይስሙኝማ!

እንደሚገባኝ ከሆነ፣ ESAT በግለሰቦች መዋጮ የተቋቋመና የሚተዳደር የግል የሚዲያ ተቋም ነው። ለዓመታትም ልክ እንደ OMN የኢትዮጵያ ሕዝብ ጆሮና ዓይን ሆኖ፣ ወገኖቻችን ከሌላ ምንጭ ሊያገኙ የማይችሏቸውን አሳሳቢ ጉዳዮችን ለሕዝብ ሲያደርስ የኖረ ድርጅት ነው። በዚህ ሥራውም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተዓማኒነት አግኝቷል። አንዳንዴ ግን ልክ እንደ ማንኛውም የሚዲያ ተቋም “ስህተቶችን” ሲፈጽም ተስተውሎዋል። አዎ! የሚዲያ ተቋማት በተለይም ካገር ውጭ ሆነው የሚሰሩ ከሆነ አልፎ አልፎ የተሳሳተ መረጃ ለህዝብ ሊያደርሱ ይችላሉ። ተቋማቱ የሚገመገሙት ግን ባሰራጪቸው የተሳሳተ ዜና ልክ ሳይሆን፣ ያስተላለፏቸው ዜናዎች በተሳሳተ ማስረጃ የተደገፉ ወይም ከተሳሳተ ምንጭ የተቀዱ መሆናቸውን ወዲያውኑ ለሕዝብ አሳውቀው ይቅርታ በመጠየቃቸው ነው። “በስህተት የሚተላለፈው” ዘገባ ግን በተደጋጋሚ የሚያነሳው አንድን ጉዳይ ወይም በአንድ ቡድን ላይ ያተኮረ ከሆነ፣ የሚዲያ ተቋሙ ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል ማለት ነው። በዚህ መልኩ ESAT የብቃት ወይም የአቋም መመዘኛውን መስፈርት አያሟላም ባይ ነኝ። እስዎ ዝም ብለው ያላንዳች ማስረጃ OMNን ከ RTLM ጋር

እንዳያያዙት ሳይሆን ሁለት ተጨባች መረጃዎቼን ብቻ ላቅርብና ከ ESAT እና ከ OMN የትኛው የተሳሳተ መረጃ ሆን ብሎ ለአድማጮች በማቅረብ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ለማጋጨት ጥረት እንደሚያደርግ እንይ። በነገራችን ላይ ይህንን "ክሴን" ሳቀርብ ዓላማዬ ከስዎ ለየት ያለ ነው። እኔ ESAT እስከ ዛሬ ባቀረባቸው "የጥላቻ ንግግሮች" ወይም "አንድን ብሄር በሌላው ላይ ለማነሳሳት" ሆን ብሎ ስለፈጸማቸው የወንጀል ተግባራት ምክንያት ይከሰስ ወይም ተቋሙ ይዘጋ የሚል ዕብደት አይከጅለኝም። የግል ሚዲያ ባልተለመደበት ኋላ ቀር አገራችን እንደ ESAT እና OMN ያሉ ሌሎችም ተጨማሪ የግል ሚዲያ ተቋማት ያስፈልጉናል። ዋናው ነገር፣ የተቋሙ ሠራተኞች፣ ከመጀመርያው በሙያቸው የተካኑ እንዲሆኑ፣ ወገንተኝነት እንዳያጠቃቸውና ሆን ብለው የተሳሳተ ወይም የተጣመመ መረጃን ለሕዝብ እንዳያቀርቡ፣ በድንገት የተሳሳተ መረጃ ካቀረቡ ደግሞ ወዲያውኑ ይቅርታ የሚጠይቁ እንዲሆኑ ማሳሰብ የኛ ኃላፊነት ይመስለኛል። ወደ ክሶቼ ልመለስና!

ESAT አውቆ በድፍረትም ሆነ ሳያውቅ በስሕተት፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ለከፍተኛ ግጭት ሊዳርግ የሚችል የጥላቻ መልዕክት አስተላፏል የምላቸውን ሁለት ማስረጃዎቼን ላቅርብ፣

> ***<u>ማስረጃ አንድ፣</u>*** በሃምሌ ወር 2008 ዓ/ም ከአማራ ክልል "በጽሁፍ" የደረሰውን "ትኩስ ዜና" ታውቂው የ ESAT ጋዜጤኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላለፈው ዜና፣ የአማራ ሕዝብ በወያኔ ላይ ስላወጀው ጦርነት ያወሳና፣ "የትግራይ ሕዝብ ወያኔ እንደማይወክለው ተረድቶ ከአማራ ወንድሞቹ ጎን ተሰልፎ የወያኔ ኤሊቶችን እንዲወጋ የቀረብለትን ጥሪ ችላ ማለቱ አልበቃ ብሎት፣ "ልጆቻችን ስለሆኑ ከጎናቸው አንለይም" በማለታቸው "ወደድንም ጠላንም ምርጫው አንድ ብቻ ነው፣ ..... **የተበላሸን ዓሳ ከባሕር ማስወገጃ መንገዱ አንድ ነው፣ የባሕር ውሃን ማስወገድ ነው**!" ብለው መወሰናቸውን ለህዝብ "አብስሯል"። በቀላል አማርኛ፣ ወያኔን ለመደምሰስ የአማራ ሕዝብ ያለው ብቸኛ አማራጭ የትግራይን ሕዝብ መደመሰስ ነው ማለት ነው። ባንድ ሕዝብ ላይ የጅምላ ግድያና ጭፍጨፋ ማወጅ ማለት ትርጉሙ ይኸው ነው። አዎ! የ ESAT አመራር፣ የተላለፈው መልዕክት በስህተት መሆኑን አምኖ ከድህረ ገጻቸው ላይ ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ አንስተውታል። ግን ዘግይተዋል። በዛሬ የቴክኖሎጂ ዘመን፣ መረጃ አንዴ ካፍ ከወጣ መመለስ የማይቻልበት ጊዜ ስለሆነ ይኸው እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ ድረ ገጾች ላይ ተለጥፎ፣ የትግራይ ሕዝብም በሰማው ቁጥር በ ESAT ላይ ያለውን የጥላቻ ትኩሳት እየጨመረ ሲሄድ፣ እኔም ለማስረጃነት ይኸው እየተጠቀምኩበት ነው። ደግነቱ ግን ከዓቅም ማነስ ይሁን ወይም በሆነ ተዓምር ምክንያት በትግራይ ሕዝብ ላይ የታወጀው የጅምላ ጭፍጨፋ አልተተገበረም። "በቀጥታ ካገር ቤት እንደደረሰን ያስተላለፍነው ዜና ስለሆነ ይዘቱን ለመርመር ጊዜ አላገኘንም" የሚለው የ ESAT ማስተባበያ ግን ውኃ አይቋጥርም። ጋዜጤኛው "የተላከለትን ጽሁፍ" ስቱዲዮ ቁጭ ብሎ ከማንበቡ በፊት የድርጅቱ የተክኖሎጂ ባለሙያዎች ከደብዳቤው ይዘት ጋር የሚጣጣም ቪዲዮዎችን ከESAT መዝገብ ቤት ጎልጉለው በማውጣት ከንባቡ ጋር አዋህደው ስላቀረቡ፣ "የተሳሳተ መረጃው" ለሕዝብ የደረሰው ይዘቱን ለመመርመር ጊዜ አጥሮን ነው የሚለውን "ምክንያታቸውን" ውድቅ ያደርግባቸዋል።
>
> > ***<u>ማስረጃ ሁለት፣</u>*** በሶማሊያ ክልልና በአጎራባቹ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች መካከል በተፈጠረው ግጭት ሳቢያ የብዙ ዜጎች ነፍሳት መጥፋቱ የሚታወስ ነው። ግጭቱን አስከትሎ ቁጥራቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሁለቱም ብሄር ተወላጆች ተፈናቅለዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ESAT ኖቬምበር ወር 2018 ዓ/ም፣ የብዙ ሰዎች ሬሳ ባንድ ላይ ተከምሮ የሚያሳየውን ዘግናኝ ቪዲኦ ለሕዝብ አቅርቦ፣ ሬሳው የሶማሌዎች ሲሆን ገዳዮቹ ደግሞ ኦሮሞዎች ናቸው ብሎ ተረከ። የቴክኖሎጂ ጠበብት ኋላ እንዳረጋጡልን ከሆነ ግን፣ ቪዲዮው፣ በሰኔ ወር ላይ በካሜሩን በተፈጠረው የርስ በርስ ግጭት ጊዜ የተገደሉትን የካሜሩን ዜጎችን ሬሳ የሚያሳይና የቪዲዮውም ኦሪጂናል ቋንቋ በካሜሩን ከሚነገሩት ቋንቋዎች አንዱ እንደ ነበር ነው። የ ESAT ይህንን የተሳሳተ ዘገባ፣ ምንጩን ሳያጣራ ለሕዝብ ያቀረበበትን ዓላማ ምን እንደሆነና ለምንስ ይህን ያህል ጥረት ተደርጎበት የኦሪጂናሉ ቪዲዮ ቋንቋ ደምስሶ በኦሮሚኛ ተካው ስለሚለው መልስ ባይኖረኝም፣ ድርጊቱ ግን ሆን ተብሎ አንድን ሕዝብ በሌላው ላይ አነሳስቶ አስከፊ ለሆነ የርስ በርስ ዕልቂት ለመዳረግ ነው የሚል ግምት አለኝ። የ ESAT "ሌሎች ያሠራጩትን ይዘቱን በደንብ ሳንመረምር ያስተላለፍነው ዘገባ ነውና ይቅርታ ይደረግልን" ማለት፣ ሰውዬውን የገደልኩት አውሬ መስሎኝ ነውና ይቅርታ ይደረግልኝ የማለትያህል ነው። የሞተ ሰው አይመለስም። በቪዲኦ ምስል የተደገፈ ዘገባ ደግሞ አንዴ ከታየ ለዘላለም በሰው አእምሮ ተቀርጾ የሚቀር ስለሆነ መልሶ እንዳልነበር ማድረግ አይቻልም። ተራ የተዛባ ወሬ ሲሰማ በሕዝቦች ሰላምና ጸጥታ ላይ የሚያደርሰው አደጋ ስለሌለ ያው ወሬ ነው ተብሎ ይታለፋል። ESAT "ሳላጣራ በስሕተት አስተላለፍኩት" ያለው የውሸት ቪዲኦ ዘገባ ዓይነት ግን በኦሮሞና በሱማሌ ክልል ኗሪዎች መካከል ሲካሄድ በነበረው ግጭት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር ነበር። የሚገርመው ደግሞ፣ ይህንን ዘገባ ተከትሎ፣ በሶማሌ ክልል ብቻ ሳይሆን በጂቡቲ በሚኖሩ ኦሮሞ ስደተኞች ላይ የደረሰውን እልቂት ቢቢሲ በጥልቅ ሲዘግበው፣ ESAT ግን "አልሰማሁም" አለ።

በዛሬው ያገራችን ሁኔታ ሁሉም ነገር በብሄር መነጽር ብቻ በሚታይበት ሰዓት ይኸኛው ወይም ያኛው ህዝብ በዚህኛው ወይም በዚያኛው ላይ ይህንን ወይም ያንን ወንጀል ፈጽሟል ብሎ የተሳሳተ መረጃን ማቅረብ፣ በቀላሉ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የሚያጋጭ መሆኑ ታውቆ ESATም አስፈላጊውን ዕርምት ያደርጋል ብዬ አምናለሁ። በየርስ በርስ ግጭት አሸናፊ ስለማይኖር፣ ከዚህ ሕዝብን በሕዝብ ላይ የማነሣት እኩይ ተግባር ተቆጥበን መላው ያገራችን ሕዝብ እኩል አሸናፊ የሚሆንበትን ጎዳና ብንቀይስ ለሁሉም ይጠቅማል ባይ ነኝ። ጊዜያችንን አጥፍተን ለጥፋት የሚረዳን ምስል እያቀረብን ሕዝብን በሕዝብ ላይ ለማነሳሳት ወይም በሕዝቦች መካከል ጥላቻን ከመዝራት ይልቅ፣ ያንኑ ጭንቅላት ለበጎ ተግባር ብናውለው አገራችን ምንኛ በተጠቀመች! በሆነ ምክንያት ጭንቅላታችንን ለበጎ ነገር ማዋል ካቃተን ወይም ካልፈለግን ደግሞ ከዚህ ከባሕር ማዶ የሞቀ ቤታችን ቁጭ ብለን በቴክኖሎጂ ዕርዳታ የተሳሳተ ምስልን፣ የችግር ቅርጫትን ተሸክሞ ማራገፊያው ጠፍቶት እያቃሰተ ላለው ወገናችን አቅርበን ለርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳሳ ከመቀስቀስ ብንቆጠብና ዝም ብለን ባጋጣሚ ያገኘነውን ሰላማዊ ኑሮያችንን እዚሁ ባህር ማዶ ሆነን ማጣጣሙን ብንቀጥልበት የተሻለ ነው ባይ ነኝ።

ውድ ሻለቃ! **"Ethiopia: A country on the Brinks"** የሚለው ሁለተኛው ጽሁፍዎ ከሞላ ጎደል ከላይ ባነሳኋቸው ነጥቦች ዙርያ ያሉትን ጉዳዮች በድጋሚ የሚያነሳ ስለሆነና በበኩሌ እንደተሰማኝ መልስ ስለሰጠሁባቸው እንደገና ማንሳቱ አስፈላጊ አይመስለኝም። ሆኖም ግን በዚህኛው ጽሁፍዎ እጅግ በጣም ያሳሰበዎት የኢትዮጵያ ወደ ጥፋት አፋፍ ላይ መድረሷን ስለሆነ በዚሁ "አሳሳቢ ጉዳይ" ዙርያ ያነሷቸውን አንዳንድ ነጥቦች ላንሳ! አዎ! እስዎም እንዳሉት፣ ያገራችን ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው ያለው። ሆኖም ግን፣ ከላይ የተጠቀሱት ወቅታዊ ችግር እንዳሉ ሆነው እንደስዎ ያሉ አንዳንድ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ከውጭ ሆነው በሕዝቦች መካከል የሚዘሩት መርዝ፣ አሳሳቢ የሆነውን አገራዊ ጉዳይ ይበልጥ አሳሳቢ እንዲሆን አድርጎታል ብዬ እገምታለሁ። እስቲ ካነሷቸው ነጥቦች ጥቂቶቹን አጠር ባለ መልኩ ልፈትሽ!

***ሀ***) ኢትዮጵያ የወደቀች (የፈረሰች) አገር ናት አሉን ሻለቃ በድፍረት! "የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዛሬ ደካማ ሆኖ አያውቅም" ለዚህም ምክንያቱ፣ ይላሉ ሻለቃ፣ የዶ/ር ዓቢይ አዴፓን ላለማስቆጣት ብሎ የብሄር ካርድ መጫወቱና ወደ አሮሞ ማጋደሉ፣ ይባስ ብሎም ለዚህ ድብቅ የኦሮሞ አጀንዳው መተግበር የሚረዳ ጓደኛውን ጀዋርን ከውጭ አገር ጋብዞ ማምጣቱ፣ ፓታቲ ፓታታ ይሉናል። እስዎን እንደ ዲያብሎስ መልዕክተኛና የጥፋት ሐዋርያ ቆጥሬ፣ የማርያም ብቅል እየፈጨሁ ነው ብዬ ለማለፍ ፈልጌ ነበር። ግን ደግሞ እንደ ምክንያት ያቀረቧቸው አንዳንዶቹ ለምሳሌ፣ የኤኮኖሚው ድቅቀት፣ በየቦታው በመከሰት ላይ ባሉት የርስ ብርስ ግጭቶች ምክንያት የብዙ ዜጎች ከቄያቸው መፈናቀል፣ በቂ የጤና አገልግሎትና የምግብ አቅርቦት አለመኖር፣ የብዙ ዜጎች ካገር መሰደድ ወዘተ ኮለል ብለው የሚታዩ ዕውኔታዎች ስለሆኑ ዓይኔን ጨፍኜ ጆሮዬን ደፍኜ ለማለፍ አልፈለግሁም። ሌሎች ግን ለምሳሌ፣ የመከላከያና የጸጥታ ሠራዊቱ ከማዕከላዊው መንግሥት ቁጥጥር ውጭ መሆን፣ የፖሊቲካ ምህዳሩ መጥበብ ወዘተ የሚሉት ግን ዝም ብሎ የፖለቲካ ትኩሳትን ለመጨመር ያስታከኳቸው ስለሆነ በዚህ ላይ ጊዜ ማጥፋት አስፈላጊ አይመስለኝም።

በዚህኛው ክፍል ካቀረቧቸው "ምክሮች" ምናልባትም የጽሁፍዎ ዓላማም ነው ብዬ የምገምተው፣ ኢትዮጵያንና ራሱን ለማዳን ከፈለገ ዶ/ር ዓቢይ መፈጸም አለባቸው ያሉትን ሶስት አማራጮችን ናቸው። እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የሚሰማዎትን ለመናገርና ለመጻፍ እንዲሁም ለመምከር ያለዎት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እነዚህን ሶስት አማራጮች ግን ተደርድረው ሳያቸው፣ ከአንድ ተቆርቋሪ አእምሮ ሳይሆን ከአንድ ወራሪ ኃይል አፈቀላጤ ወይም የሰፈር ሟርተኛ የሚመነጭ ነው የመሰለኝ። እስዎ እያሉን ያሉት፣ ዶ/ር ዓቢይ ኢትዮጵያና ራሱን ለማዳን ከፈለገ፣

1) በእውነት ኢትዮጵያን የሚወድ ከሆነ ብቁ መሪ አለመሆኑን አውቆ የሥልጣን በትሩን ለአንድ አማራ ወይም ኦሮሞ ላልሆነ ግለሰብ አስረክቦ በአስቸኳይ መሰናበት አለበት፣ ይህን አልቀበል ካለ ደግሞ፣
2) ህገ መንግሥቱን አፍርሶ፣ ፓርላማውን በትኖ በዓዋጅ የሚተዳደር ጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣ ይህንንም ካልተቀበለ ደግሞ፣
3) ሳይወድ በግድ የሽግግር መንግሥት አቋቋሞ በአፍሪካ አንድነትና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጥብቅ ቁጥጥር ሥር የሚካሄድ ምርጫ ማካሄድ ነው በማለት ለዘመናት ካለዎት ልምድ ተነስተው ምክርዎን ለገሱን።

ስለ ዶ/ር ዓቢይ የብቃት ማነስ ወይም ሙላት ሁላችንም የየራሳችን ግምት ያለን ስለሆነ እሱን ለውይይት ማቅረቡ አስፈላጊ አይደለም። ሆኖም ግን ዛሬ አገሪቷ ባለችበት ሁኔታና ማህብረሰቡን እንወክላለን የሚሉት ምሁር ተብዬዎች እንኳን ሳይቀር ተስማምተው በጋራ አገርን ለማስተዳደር ይቅርና በሠለጠነ መንገድ ልዩነታቸውን አቻችለው አብሮ መጓዝ ባልቻሉበት ሁኔታ፣ ለአማራጭነት የሚቀርብ አንድም በሳል የፖሊቲካ ድርጅት በሌለበት አገርና፣ በየክልሉ የማንነት ጥያቄ ብሎም በሕዝቦች መካከል "በውክልና የሚካሄድ ጦርነት" ማለትም በአክቲቪስቶችና በፖሊቲካ ድርጅቶች ከርቀት የሚመራ "የርስ በርስ ጦርነት" (localized proxy war) ከመቼውም በላይ ተስፋፍቶ እያየን፣ ዶ/ር ዓቢይ ሥልጣን ይልቀቅ ማለት፣ የሆነ የግል ጥቅም

ማስጠበቂያ ለፈፋ ይመስለኛል። በመጀመርያ ደረጃ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ ያላንዳች ደም መፋሰስ ጥገናዊ ለውጥ በመካሄድ ላይ እንዳለ ከስዎ የተሰወረ አይመስለኝም። ግን እስዎ የለመዱት የሥልጣን ሽግግር ዘዴ፣ አዲሱ ቡድን በትረ ሥልጣኑን በጉልበት ይዞ፣ የፊተኛው ሥርዓት ተጠቃሚዎች ናቸው የተባሉትን ደግሞ በጅምላ ገድሎ፣ ህገ መንግሥትንና ፓርላማውን አፍርሶ በጊዜያዊ ዓዋጅ የሚተዳደር መንግሥት ማቋቋም ስለሆነ እንደዚህ ዓይነት ሰላማዊ ሽግግር “ፈጣንና አመርቂ” መስሎ አልታይዎት ብሎ ይሆናል። አይፈረድብዎትም ሻለቃ፣ ያኔ እስዎና ጓደኞችዎ የአጼዉን መንግሥት ገልብጣችሁ በትረ ሥልጣኑን የጨበጣችሁት ልክ ዛሬ ዶ/ር ዓቢይን አድርግ ብለው በሚመክሩት የሥልጣን መያዣ ዘዴ ነበር። የእስዎ ቡድን ጃንሆይን ከሥልጣን ካወረደ በኋላ፣ “አገሪን ከመፈራረስ ለማዳን” በመጀመርያ ደረጃ በአስቸኳይ ከወሰዳቸው እርምጃዎች ጥቂቶቹ፣ ፓርላማውን መበተን፣ ሕገ መንግሥቱን ማፍረስ፣ አስቸኳይ ጊዜያዊ ዓዋጅ ማወጅና ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ማቋቋም ነበር።

ደግሜ ላስታውስዎትና ሻለቃ፣ በስዎ የደርግ መንግሥትና በዶ/ር ዓቢይ የለውጥ ቡድን መካከል ትልቅ የአሰራር ልዩነት አለ። የስዎ መንግሥት ያው እንደሚያውቁት ወጣቱንና ምሁሩን “ከኔ የተለየ አስተሳሰብ ታስተናግዳላችሁ” ብሎ በጅምላ ይጨፈጨፍ ነበር። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን እስር ቤት ማጎሩ አንሶ በታሪካችንም ሆነ በባህላችን ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቀውን “ማሰቃየትን” (torture) ወዳገራችን አስገባ። ድርጊቱን መደበኛ የሙያ ዘርፍ አድርጎ ሰዎችንም አሠልጥኖ አሰማራ። በታሪካችንም ጥቁር ነጥብ ሆኖ ቀረ። ዛሬ ያለው የለውጥ ቡድኑ ግን፣ በግፍ የታሰሩትን በገፍ ፈታ፣ የሙያተኛ አሰቃዮች ሰለባ የሆኑትን በሙሉ ፈትቶ ይቅርታ ጠየቀ፣ ካሁን በኋላም በምድሪቷ አንድም የፖሊቲካ እስረኛ አይኖርም አለ፣ ቃሉንም ጠበቀ፣ ተፎካካሪ እንጂ ተቃዋሚ የለም ብሎ የፖሊቲካ ምህዳሩን አሰፋ፣ ከዚህ በፊት በተለያየ ወንጀል የተጠረጠሩ፣ በተቃዋሚነት ወይም ሽብርተኝነት ተፈርጀው ወደ አገር ቤት መግባት ያልቻሉ ለምሳሌ እንደ እስዎ ዓይነቱን ዜጋ ወደ እናት አገራቸው እንዲመለሱ በር ከፈተ። ያሁኑ የለውጡ ቡድን የመረጠው ጎዳና ግን እስከዛሬ ሄደንበት የማናውቀው ስለሆነ በሰላም ተጉዘን እንጨርሰዋለን ወይስ መሃል ላይ በአውሬዎች እንበላለን የሚለው ሥጋት አግባብ ያለው ሲሆን፣ በዚህ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ግን ከአንድ ጥገናዊ ለውጥ ከሚያካሄድ መንግሥት ከዚህ የላቀ ውጤት መጠበቅ በአብዮታዊና ጥገናዊ ለውጥ መካከል ያለውን ልዩነት ካለማወቅ የሚመነጭ ነው ብዬ እገምታለሁ።

ሻለቃ! እንደው ስለትዎ ሰምሮ ዶ/ር ዓቢይም በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ እንበልና፣ ዛሬ ባለው ሁኔታ እንዴት ተደርጎ ነው ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የሚቻለው? በቅርጽና በይዘትም እንዲሁም በዓላማ ከማይገናኙት የአገሪቷን 107 የፖሊቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች በተወጣጡ ተወካዮች ወይስ በተለምዶ “ያገር ሽማግሌዎች” “አስታራቂዎች” ተብለው የሚታወቁትን ግለሰቦች ሰብስቦ ጊዜያዊ መንግሥት እንዲያቋቁሙ በመጠየቅ? ሻለቃ! እስቲ ሰከን ብለው ያሰፈሯቸውን ምክሮች እንደገና ይገምግሙ። ያኔ ያኔ በስዎ መንግሥት ዘመን የነበረው በመንፈስ ብቻ የኖረ “አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ” የሚለው አባባል እኮ ከቀረ ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ ሆኖታል፣ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ቢያንስ ቢያንስ አስር ዓይነት ብሄራዊ ባንዲራዎች የሚውለበለቡባትና አስር ዓይነት ብሄራዊ መዝሙር የሚዘመርባት አገር ሆናለች። ያም አልበቃ ብሎ አንዳንዶች ብሄሮችም እኛም እንደሌሎቹ የራሳችን ክልልና የራሳችን ባንዲራ ያስፈልገናል ብለው የሙብት ጥያቄ እያቀረቡ ነው። እስከ ዛሬ በአማራነታቸው የምናውቃቸው ቅማንትና አገውን የመሳሰሉ ሕዝቦች ደግሞ እኛ ለዘመናት ማንነታችንን ተገፍፈን በአማራ ተገዝተናል ብለው የራሳቸውን ፖሊቲካዊ ፓርቲ አቋቁመው ለሙብታቸው ሙግት ከጀመሩ ሰንብተዋል። ታዲያ በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ዘመን ሻለቃዬ እንዴት ተደርጎ ነው የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የሚቻለው? እንደው በውነት ስለ እውነት በዛሬው ሁኔታ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅቡልነት ሊያገኝ የሚችል ከዶ/ር ዓቢይ የተሻለ አካል ወይም ቡድን ይኖራል ብለው ይገምታሉ? እንኳን ለሁሉም የሚመች የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ይቅርና ስለሚቀጥለው የሕዝብ ቆጠራ እንኳ ሲነሳ፣ ገና ቆጠራው ሳይጀመር፣ እየተነሳ ያለው “የማንነት ጥያቄ” ያንዳንድ ብሄሮችን ቁጥር ሊያሳንስ ይችላል በሚል ግምታዊ ሥጋት ምክንያት ውጤቱ ብዙ “ፖሊቲከኞችን” ካሁኑ እያሳሰበ መሆኑን የሚያውቁት ይመስለኛል።

**ለ)** ከጽሁፍዎ እንደተረዳሁት፣ እንቅልፍ ከነሱዎት <u>ግምታዊ</u> ችግሮች አንዳንዶቹ፣ የዶ/ር ዓቢይ “ጓደኛውን” ጃዋርን ከአሜሪካ አምጥቶ OMNን ሕጋዊ ህልውና መስጠቱ፣ የዶ/ር ዓቢይ ከጃዋር ጋር ያለው የድብቅ ግንኙነት፣ የቄሮዎች ኢንተርሃምዌን በመሰለ መልኩ ግድያንና ዘረፋን ለማስፋፋት በጃዋር መመልመላቸው ወዘተ ናቸው። የዶ/ር ዓቢይን ከጃዋር ጋር ያለውን ግልጽም ሆነ ድብቅ ግንኙነት በተመለከተ ምንም ማስረጃ ስለሌለኝ አስተያየት ከመሰንዘር ብቆጠብ ይሻለኛል። ሁለቱንም በግል ስለማላውቃቸው፣ በግምት ብቻ “ይህ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው” የሚለውን መላ ምት ለመጠቀም አልፈልግም። በግሌ እንደ አንድ ተመልካች በቁርጠኝነት ለማለት የምችለው ግን፣ ዶ/ር ዓቢይ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ በብዛት የማይወደደው በኦሮሞዎች መሆኑን ነው። ገና ሥልጣን ላይ እንደወጣ በስምንቱም ክልሎች እና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በነቂስ ወጥተው “ተደምረናል” ብለው ለድጋፍ ሰልፍ ሲወጡ አብዛኛው የኦሮሚያ ክልል ሕዝብ ግን ለድጋፍ ሰልፍ አልወጣም። በቅርቡ ወደ ትውልድ መንደሬ ምዕራብ ወለጋ በተጓዝኩ ጊዜ ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር ሕዝቡ እንዳለ ኦቦ ለማንና ዶ/ር ዓቢይን

መቀየሙን ነው። እንደ ቀልድ አስመስለውም በየቦታው “ዓቢይ እኮ ትኩረቱ አማቾቹ ላይ ነው” የሚለውን አባባል ሲደጋግሙት አስተውያለሁ። ዶ/ሩ ሥልጣን ከያዙ ወዲህም ለመጀመርያ ጊዜ በአደባባይ ወጥቶ የተቃውሞ ሰልፍ ያደረገውም በዋሺንግቶን ዲሲ የሚገኝ የኦነግ ደጋፊ ቡድን ነው። ስለዚህ ዶ/ር ዓቢይ “የብሄር ካርታ” እየተጫወተ ነው ብለው ሲጽፉ እንደተለመደው በማስረጃ ተደግፈው ሳይሆን “ኦሮሞነቱን” ብቻ ዋቢ አድርገው ይመስለኛል።

ሻለቃ! ዶ/ር ዓቢይንም ሆነ ጃዋርን በግል አላውቃቸውም፣ እነሱም ምን ያህል እንደሚተዋወቁ አላውቅም፣ ሁለቱም በየሚዲያው ከሚሰጡት መግለጫና አስተያየት ተነስቼ፣ እንዲሁም ሚዲያዎች ስለሁለቱ በየገጻቸው ከሚለጥፉት ተነስቼ ስገመግም ግን ሁለቱን ግለሰቦች የሚያገናኛቸው በርግጥም የሆነ ነገር አለ። በመጀመርያ ደረጃ ሁለቱም ሰዎች ናቸው። የሁለቱም ያባቶቻቸው ስም ከዓረቢኛ የተወሰደ ነው፣ የሁለቱም እናቶች ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ) ሲሆኑ አባቶቻቸው ደግሞ ሙስሊሞች ናቸው፣ ዶ/ር ዓቢይም ጃዋርም ተጋብተው፣ ቤተሰብ አፍርተው አብረው የሚኖሩት ከክርስቲያን (ፕሮቴስታንት) ባለቤቶቻቸው ጋር ነው። ይህ ያጋጣሚ ግጥጥሞሽ ግን ምን ያህል በፖሊቲካ ሕይወታቸው ላይ ጫና እንዳሳደረና የሁለቱን ፖሊቲካዊ አስተሳሰብ አቀራርቦ ለወዳጅነት እንዳበቃ እስዎ ብቻ የሚያውቁት ይመስለኛል። እንደሚመስለኝ ግን፣ ሻለቃ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ ፍጡሮችን ባንድ ቅርጫት ውስጥ ከትቶ ባንድ ላይ የፈረጁት፣ በግልዎ ከነበረዎት የአስተዳደርና አመራር ተሞክሮ ይመስለኛል። ይኸ፣ አንድ ግለሰብ ያልሆነውን “ነህ” ብሎ ሲፈረጅ፣ ተፈራጁ ግለሰብ ደግሞ በተቻለውን መጠን “አለመሆኑን” ለማስረዳት ቢሞክርም፣ ፈራጁን አካል ማሳመን ከአቅሙ በላይ ሲሆንበት ደግሞ “ስሜ መጥፋቱ ካልቀረ” ብሎ “ያልነበረውን ለመሆን” ይወስናል። ያስታውሱ እንደሆን ሻለቃ፣ ያኔ በስዎ መንግሥት ጊዜ፣ የትግራይና የኤርትራን ወጣት በሙሉ ወያኔና ሻዕቢያን ትደግፋላችሁ ብላችሁ በመፈረጃችሁና ብሎም በማሰቃየታችሁ፣ “ስማችን መጥፋቱ ካልቀረ” ብለው አብዛኞቻቸው በርግገው ጫካ በመግባት “የጠላትን ጎራ” እንዳሳበጡ መቼውም የሚረሳዎት አይመስለኝም። ወያኔም እንደዚሁ፣ ኦሮሞ ሆኖ ስለ ኦሮሞ ሕዝብ መብት ለማንሳት የሚሞክረውን ወጣት በሙሉ “የኦነግ ደጋፊ ናችሁ” ብሎ ስላሰረና ስላሰቃየ፣ ስማችን መጥፋቱ ካልቀረ ብለው ብዙዎቹ ወደ ጫካ ሄደው ኦነግን በመቀላቀል የድርጅቱን ታጣቂ ኃይል ቁጥር አሳበጡ። ስለዚህ ሻለቃዬ፣ ሰዎችን በሚያምኑበት ወይም በሚያስተናግዱት አስተሳሰብ ሳይሆን፣ በብሄር መነጽር ብቻ መዝኖ፣ ወይም ከስማቸው ብቻ በመነሳት፣ ይህኛው “ኦነግ” ነው ወይም “ኦነግን ይደግፋል” ወይም ይኸኛው ደግሞ “ወያኔ” ነው ብሎ መፈረጁ፣ ትርፉ “የጠላትን” ጎራ ከማጠናከር ባሻገር የባሰ ክፍፍል ያመጣ እንደው እንጂ የማያሰባስብና ለመንግሥትዎ ሆነ ለወያኔም ያልሠራ ተሞክሮ ነውና እሱን የሙጥኝ ብሎ ለመተግበር መሞከር ትርፉ ጥፋት ብቻ ይመስለኛል።

*“The Qeros are recruited by Jawar to do the dirty work of killing, plundering and creating an atmosphere of fear in the nation”* በማለት “ቄሮዎች ለግድያና ለዘረፋ ወንጀል በጃዋር እንደ ተመለመሉና የሥጋትና ፍርሃት ድባብ ባገሪቷ ላይ እንዳሰፈኑ” አድርገው ማቅረብዎ ደግሞ ከስዎ የማይጠበቅ ደረጃውን ያልጠበቀ ተራ አነጋገር ነው። ለዘመናት “ተጋብተን ተዋልደን አብረን በሰላም የኖርን” እያሉ ሲለፍፉ፣ እንዴት የወንድሞችዎንና የአማቾችዎን (ኦሮሞዎችን ማለቴ ነው) ወግና ባሕል ትንሽ እንኳ ሳያውቁ እስከ ዛሬ እንደኖሩ ሳስበው ይደንቀኛል። ቄሮን፣ እንደ ጀዋር ያሉ ግለሰቦች ለራሳቸው ዓላማ ማራመጃ ብቻ ጠፍጥፈው የሚሠሩት፣ ማህበረሰባዊ ኃላፊነትና ሚና የሌለው የወጣቶች ስብስብ አድርገው ሲጽፉ ምን ያህል የኢትዮጵያን ሕዝቦች ማንነት የማያውቁ መሆንዎን በተግባር አረጋግጠውልናል። አይፈረድብዎትም! ያደጉበትም ሆነ በቁንጮነት ያገለግሉ የነበረው ሥርዓት፣ ያገሪቷ ሕዝቦች ካንድ ሸክላ የተጠፈጠፉና አንዳችም ዓይነት የራሳቸው የሆነ ባሕልና ወግ የሌላቸው፣ ቢኖራቸውም ደግሞ እሱን ትተው በአንድ ግምታዊ የሆነ “ኢትዮጵያዊ” ባህልና ወግ ውስጥ እንዲቀልጡ ያስገድድ ነበርና፣ ከዚያ አንጻር ሲታይ የስዎ “የዋህነት” እምብዛም ባላሳሰበ ነበር። የሚያሳስበው ግን፣ እንደዚህ ዓይነቱን መሠረታዊ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ማህበረሰባዊ አስተዳደር፣ ወግና ባሕል ሳያውቁ እንዴት “አገሪቷን ከጥፋት ለማዳን” ይህኛው ወይም ያኛው አካሄድ ይሻላል ብለው ለመምከር ድፍረት ማግኘትዎ ነው። ሻለቃዬ፣ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛልና እንደ አንድ አዛውንት ምክር ልለግስ ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ ትምሕርት የዕድሜ ገደብ የለውምና በቀሪው ዘመንዎ የቄሮን ማንነት በደንብ ለመረዳት ለቄሮ - 101 ኮርስ ካሁኑ ቢመዘገቡ ጥሩ ነው እላለሁ። እስከዚያ ድረስ ግን ለመንደርደርያ ይሁንዎት ዘንድ የሚከተለውን ላካፍልዎት!

በኦሮሞ ሕዝብ ባሕል መሠረት፣ ቄሮ ማለት በአንድ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ትውልድ ነው፣ አብዛኞቹ በዚያ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንዶች፣ ያላገቡና በአካል ጥንካሬ ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት የላቁ ስለሆነ፣ የማህበረሰቡን ሕልውና ከሚያሰጋ የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሠራሽ አደጋ ለመከላከል ሁሌም ዝግጁ የሆነ ትኩስ ጉልበት ያለው ወጣት ነው። ባጭሩ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና ማሕበረሰቡን ከተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ጥቃት ለመከላከል እንጂ የሌሎችን መብት ለመጣስ አይደለም። በኢትዮጵያም ቄሮዎች የተጫወቱት ሚና ይህንኑ ነበር። ከሌሎች ለውጥ ፈላጊ ወገኖች ጋር በግንባር ቀደምትነት ተዋግቶና መሥዋዕት ከፍሎ ግፈኛውን ወያኔ መራሹን መንግሥት አንበርክኮ ለዛሬው ጥገናዊ ለውጥ ያበቃን የተደራጀ አካል ቢኖር ይህ ዛሬ እስዎ “ለግድያና ለዘረፋ የተመለመለ ወንጀለኛ ቡድን” አድርገው የሚያቀርቡት ቄሮ ነው።

ሌላው ይቅርና እስዎንና መሰሎችዎን ለዓመታት  ከተደበቃችሁበት ዋሻ በክብር ወደ እናት አገራችሁ እንድትመለሱ ያደረጋችሁ ይኸው ቄሮ ነው። ከዚህ ውጭ የተስተዋለ ድርጊት ካለ ግን፣ ፈጻሚው ሌላ ወንጀለኛ አካል እንጂ ቄሮ አይደለም ለማለት ነው። ገባዎት?

ዛሬ ዛሬ ለምን የቄሮ ክፋት እንደታየዎት አልገባ አለኝ እንጂ ሻለቃ፣ ትናንት ይኸው ወጣት ትውልድ እኮ ነው የወያኔ መራሹን መንግሥት በመቃወም በሰልፍ ወጥቶ መንገዶችን ሲዘጋና ሕዝቡን ከዳር እስከዳር አስተባብሮ ለሕዝባዊ ዓመጽ ሲያነሳሳ “ጎበዞች በርቱበት” ስንል የነበረው። በዚያ ከዳር እስከዳር በተቀጣጠለው የአመጽ እሳት በኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ የአማራ ብሄር ተወላጆችም ሆነ ንብረታቸው ላይ አንድም ቦታ ጥቃት ባለመድረሱ ከልባችን ያመሰገንነውና ያደነቅነው ቄሮ፣ ዛሬ በምን ምክንያት ነው በጃዋር የተመለመሉ ወንጀለኞች ተደርገው የተቆጠሩት? በዚያ በቀውጢ ቀን በወንድማማችነት መንፈስ ደረቱን ነፍቶ “ጣናን ኬኛ” ብሎ ባህር ዳር ድረስ ተጉዞ ከአማራ ወታት ጋር ሆኖ እምቦጭን ለመንቀል በቁርጠኝነት የተሰለፈውን ቄሮን፣ ዛሬ ምን ቢፈጠር ነው ያ ሁሉ በጎ የትብብር መንፈስ እንዳልነበር ሆኖ ቄሮዎች በግለሰብ የተመለመሉ ነፍሰ ገዳዮች ተደርገው የተቆጠሩት? ሻለቃዬ! ምክንያትዎ ለኔ ግልጽ ነው። ቄሮን እንደ ወንጀለኛ ቡድን ፈርጆና ዓላማውም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማጣላትና ብሎም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ነው ብሎ ሕዝባችንን በቄሮ ላይ ብሎም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ እንዲነሳሳ ለማድረግ ነው። ግን ተሳስተዋል! እስዎና መሰሎችዎ ከባሕር ማዶ ሆናችሁ ጥቃቂን ማህበረሰባዊ አለመግባባቶችን እንደ አገር አፍራሽ ጉዳይ በመቁጠር፣ ጭል ጭል በምትል እሳት ላይ ቤንዚን እየጨመራችሁ አባባሳችሁት እንጂ፣ በኢትዮጵያ ቆይታዬ ጊዜ ተዟዙሬ ያየሁት ነገር ቢኖር በኦሮሞና በአማራ፣ በአማራና በጉሙዝ ወይም በጉጂና በጌዴኦ ህዝብ፣ በአጠቃላይም በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል አንዳችም ዓይነት አለመግባባት አለመኖሩን ነው። በቡራዩ የተፈጠረውን ግጭት አንዳንዶች ለፖሊቲካ ጠቀሜታ ሲባል ካገርም አልፎ ዓለም አቀፋዊ ግጭት አስመስለው ያራግቡ የነበረውን፣ የኦሮሞና የዶርዜ ማህበረሰብ ተወካዮች ያላንዳች የውጭ አካል ጣልቃ ገብነት፣ በባሕላቸው መሠረት ቄጤማና ወተት ይዘው፣ በሬ አርደው ደም አፍሰሰው፣ ተሳስመው ቋሚ ዕርቅ አውርደው የግጭቱን ምዕራፍ ከዘጉ ወራት ቢያልፉም እስዎና መሰሎችዎ ግን ዛሬም የቡራዩን ግጭት፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለቄሮ መጥፎነት ማስረጃ በመናጀነት እየተጠቀማችሁ ሳስተውል፣ ምንኛ ጭንቅላታችሁ በክፋት ድርና ማግ የተተበተበ መሆኑን እረዳለሁ።

ሐ) ***“Despite requests by millions of Ethiopians for the closure of this media outlet (OMN), the PM has never criticized the station let alone order its closure. Thousands of Ethiopians have signed a petition to the Minnesota attorney general and US AG to ban OMN media for inciting ethnic violence in Ethiopia…”*** ይሉናል ሻለቃ! ከላይ እንዳልኩት እኔ ላለፉት አምስት ዓመታት OMNን ስከታተል በኦሮሚኛውም ሆነ በአማርኛ ፕሮግራሙ በሚተላለፉት ዜናዎችና ትንተናዎች ውስጥ አንድም ቀን የዘር ወይም የኃይማኖት ጥላቻ ያለበት ንግግር ወይም አስተያየት ሰምቼ አላውቅም። በዚያውም ልክ፣ አንድም ቀን የተሳሳተን ማስረጃን ለሕዝብ አቅርቦ ሕዝብን በሕዝብ ላይ ሲያነሳሳ አልሰማሁም አላየሁም። ከ ESAT የሚለይበት ትልቁ እሴቱም ይኸው ይመስለኛል። ያልገባዎት ነገር ግን ሻለቃ፣ እስዎ ድርጅቱን ለማዘጋት ፊርማ አሰባስበው ለአሜሪካን መንግሥት ለመላክ ሲፈጉ፣ መላው የኦሮሞ ሕዝብ ደግሞ በዘመናት ታሪኩ ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ ያገኘውን ሕዝባዊ የቴሌቪዥን ጣቢያን የፈለገውን መስዋዕት ከፍሎ ሊያቆየው ቆርጦ እንደተነሳ አለመገንዘብዎ ነው። እስዎና መሰሎችዎ፣ ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ ሌላ ቋንቋ በቴሌቪዥን ስትሰሙ የሚያሳክካችሁ፣ የራስዎንና የመሰሎችዎን ፍላጎት ለማሟላት ሲባል ብቻ OMN ይዘጋ ብላችሁ ዘመቻ ሲታካሄዱ፣ ጥላችሁ ከጃዋር ጋር ሳይሆን ከአርባ ሚሊዮን የኦሮሞ ሕዝብ ጋር እንደሆነ ብታውቁት ይጠቅማል ባይ ነኝ። “ሞቼ አግኝቼሽ ሙች አልልሽም” አለ ጎረምሳው፣ ከብዙ ጅንጀናና ልመና በኋላ ለጥብስ ያደረሳት ቆንጂት “ሙች በለኝ” ስትለው! ለዘመናት ስንመኘው፣ የታገልንለትና ሞተን ተሟሙተን ያገኘነውንና በታሪካችን የመጀመርያ የሆነውን የግል ሚዲያ፣ “ይሙት በሉት” ሲሉን “ሞተን አግኝተነው ይሙት አንለውም” እንላለን። እስዎና ደጋፊዎችዎ ደግሞ የለም “መሞት አለበት” ካሉን ደግሞ አይ! የብዙ ሚሊዮን የኦሮሞን ሕዝብ የሚጠቅምና የድካማችን ውጤት ስለሆነ፣ OMN ከሚሞትብን ምናልባት እስዎና ጓደኞችዎን ወይ ሙቱ ወይም ደግሞ አርፈው ይቀመጡ እንላለን።

እንደው ሳስበው ግን ሻለቃዬ፣ “when you are used to privileges, equality feels like opression” የሚለው አባባል በርሶው ልክ ተቀዶ የተሰፋ ይመስለኛል። ለዘመናት የለመዱት “አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ፣ አንድ ቋንቋ” ትርክት ታሪክ ሆኖ ቀርቶ በ“አንድ አገር ሰማኒያ አምስት ቋንቋ” እውኔታ ሲተካ፣ ያ እንደ አንድ አማርኛ ተናጋሪ ግለሰብ የነበረዎት “ልዩ ጥቅም” ቀርቶብዎት ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር እኩል መሆንዎ የተጨቆኑ መስሎ ቢታይዎት አይገርምም ማለቴ ነው። ይህ እውኔታ ደግሞ በምንም ተዓምር ወደ ኋላ ተቀልብሶ በስዎ “ወርቃማ ዘመን” ዓይነት ስለማይተካ፣ በቀሪው ዘመንዎ ከዚህ ዕውኔታ ጋር ራስዎን አስተካክለውና፣ ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችም ለባለቤቶቻቸው የተከበሩ ብሄራዊ እሴቶች መሆናቸውን ተረድተው የተረጋጋ ኑሮ ቢኖሩ የተሻለ ይመስለኛል። ሌላ ምርጫም ያለዎት አይመስለኝም።

***መደምደሚያ፣***

ሻለቃ! እውነትዎን ነው። የዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው። በያካባቢው የተለያዩ ብሄሮች የማንነት ጥያቄ እያነሱ ሌላ ጊዜ በሰላም ይኖሩ ከነበሩ ጎረቤቶቻቸው ጋር እየተጋጩ ነው። ሕዝብ ሳይወክላቸው የዚህ ወይም የዚያኛው ብሄር ወይም ሕዝብ ተወካይና መብት አስጠባቂ ነን የሚሉ 107 የፖሊቲካ ድርጅቶች አገሪቷን የሙዝ ሬፑብሊክ አስመስለዋታል። የኤኮኖሚው ሁኔታ አሽቆለቆለ ባይባልም አንዳችም ዕድገት የማያሳይበት ደረጃ ላይ ነው። የፊተኛው ሥርዓት ኤሊቶች ያለ የሌለ ያገሪቷን ሃብት በተቀነባበረ ዘዴ ካገሪቷ ያስወጡ ወይም በድብቅ ይዘው የተቀመጡ ስለሆነ አገሪቷ እስዎም በትክክል እንደዘገቡት፣ ለመድኃኒት መግዣ ብቻ የሚበቃ የውጭ ምንዛሪ ታቅፋ ነው ያለችው። በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፣ አበዳሪ አገሮች ደግሞ ቀደም ሲል በተዋዋሉት መሠረት ያበደሩት ገንዘብ እስከነወለዱ በአስቸኳይ እንዲመለስላቸው ይወተውታሉ። የለውጡ ቡድን ከላይ የሚያውጀው የለውጥ ነፋስ አንዲት ሴንቲሜትር እንኳ ቢሮክራሲው ውስጥ ዘልቆ አልገባም። የፍትህ ሥርዓቱ ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ በሙስናና በብቃት ጉድለት የተካነ ስለሆነ ዛሬ በቂ መረጃ እንኳ የተገኘባቸውን የትናንት ሌቦች ለፍርድ ሊያቀርብ የሚችል እጁ ንጹህ የሆነ መርማሪ ወይም ዓቃቤ ሕግ ማግኘት በጣም ከባድ እንደሆነ አስተማማኝ ምንጮች ይጠቁማሉ። ዳኝነት ይመራበት የነበረው መሪህ በልምድ የምናውቀው ዓይኗን በሸፈነችና በእጇ ሚዛን በያዘች “ወይዘሮ ፍትሕ” (Lady Justice) ሳይሆን ዓይናቸውን አፍጥጠው ጉቦ በሚጠይቁ ሙሰኞች ዳኞች ነው። ከዚያም በላይ በያካባቢው ያለው ወጣት በፍትህ ጉዳይም ላይ ይህ ነው የማይባልና ተገቢ ያልሆነ ጫና እያደረገ ስለሆነ፣ ባለፈው የወያኔ መራሹ የኢህአዴግ ጊዜ ከፍተኛ ባላሥልጣን የነበሩ ለምሳሌ እነ በረከት ስምዖን ዓይነት ተከሳሽ፣ በራሳቸው ገንዘብ እንኳ የግል ጠበቅ ለመቅጠር እየፈለጉ የክልሉ አቡካቶዎች ወጣቱን ፈርተው ፍርድ ቤት ቀርበው ሊሟገቱላቸው ፈቃደኛ ያልሆኑበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው።

አዎ! አገራችን በጽንፈኞች ተውርራለች፣ አንዱ ቡድን ከግብጽ እስከ በርበራ የነበረውን የአማራ መሬት አስመልሳለሁ ብሎ ሲያቅራራ፣ ሌላው ደግሞ ጠቅላላው ኢትዮጵያ የኩሽ ልጆች ምድር ስለሆነች፣ የሴም ዝርያ ነን የሚሉት ምንም ቦታ አይኑራቸው ይላል። አንድ ቡድን፣ አዲስ አበባ የአዲስ አበቤዎች ስለሆነች ለወደፊት አስተዳደሯ መንገድ የሚያመቻች ጊዜያዊ ባላደራ ምክር ቤት (caretaker) አቋቁሜአለሁ ሲል ሌላው ደግሞ፣ የለም አዲስ አበባ የቱፋ ሙና አገርና የኦሮሚያ እንብርት ስለሆነች መተዳደር ያለባት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ብቻ ነው ይላል። ሌላም ሌላም! እነዚህ በመሠረቱ ባላሳሰቡን ነበር። ግን ሰላማዊና የሠለጠነ አስተሳሰብን ለውይይት አቅርቦ ልዩነትን በሰላማዊ ውይይት መድረክ የመፍታት ባሕል የሌለንና እንዲኖርም ጥረት የማናደርግ ሕዝቦች ስለሆንን፣ ከላይ ያነሳኋቸውን ያስተሳሰብ ልዩነቶችን ለመፍታት ጉልበት ብቻ ፍቱን መድኃኒት ሆኖ እየታየ መምጣቱ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነገር ነው።

የለውጥ ቡድኑን አባላት በተመለከተ፣ ዶ/ር ዓቢይ፣ በጣም ወጣት በሆኑና ከዚህ በፊት በሙስናውም ሆነ በመጥፎ አስተዳደር በማይታሙ ታማኝና አገር ወዳድ ግለሰቦች የተከበበ ቢሆንም፣ ለሃያ ሰባት ዓመት ሥር የሰደደውና የበሰበሰው ቢሮክራሲ ግን እንዳለ ቁጭ ብሏል። አዲስ በሙስናና በመጥፎ አስተዳደር ያልተበከለን ትውልድ ደግሞ እንደ ዕቃ ባንድ ቀን ጠፍጥፎ ማቅረብ ስለማይችል፣ ችግሩ በቅርቡ የሚቀረፍ አይሆንም። ያለ ተራማጅ ቢሮክራሲ ደግሞ የመንግሥት ፖሊሲን በተግባር መተርጎም ስለማይቻል ከላይ በነዶ/ር ዓቢይ የሚለፈፈው አዎንታዊ ትርክት ወደ ታች ወርዶ ለሕዝብ አይደርስም። ይህንን ዕውኔታ ደግሞ፣ ዶ/ር ዓቢይም በሌላ ሰው ቢተካ፣ ቢሮክራሲው በምንም ተዓምር ባጭር ጊዜ ውስጥ ተስተካክሎ ሕዝባዊ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት የዋህነት ነው።

ሻለቃዬ፣ እንደ ማንኛችንም፣ የዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ እንዳሳሰበዎት ይገባኛል። ተወልደን ያደግንባት አገርና፣ ለራሱ ሳይማር አስተምሮን ለራሱ ሳያልፍለት ለኛ ያሳለፈልን ሕዝብ የሚኖርባት እናት አገራችን ስለሆነች ከያለንበት ሆነን ለሷ መቆርቆራችን ተፈጥሮያዊ ነው። ይህን አለማድረግ ክህደትም ይመስለኛል። ያ እንዳለ ሆኖ ግን፣ የርስዎ መቆርቆር ትንሽ መስመር የሳተና ወገናዊ የሆነ ይመስለኛል። እንደ አንድ ወታደራዊ መኮንን ያገለገሉትን የፊውዳል ሥርዓትና አንጻባራቂ ኮከብ የነበሩበትን የደርግ መንግሥትና የኢሠአፓ አመራር አባል ሆነው የኤርትራን የነጻነት ታጋዮችን ለምደምሰስ በአስመራ ያሳለፉትን ጊዜያት፣ ባገሪቷ በነበረው አንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ ከአማርኛ ሌላ አንድም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ በማይሰማበት ዘመን እስዎ እየተደሰቱ፣ ሌሎቻችን ደግሞ እንደው አንድ ቀን እኛም ይህ ዕድል ደርሶን በገዛ ቋንቋችን የሚተላለፍ የሬዲዮና የቲቪ ጣቢያ ኖሮን እያልን በተስፋ ስንጠብቅ ኖረን፣ ዛሬ ያ ህልም ዕውነት ሆኖ ከርስዎ እኩል መደሰት ስንጀምር፣ በስዎ ልክ የተሰፋውን “አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ እና አንድ ቋንቋ” ግምታዊ ሱሪ ሁላችንም እንድንለብስ ማሰብዎ ምንኛ ከለውጡ ጋር ራስዎን ለማላመድ እንደተቸገሩ ያሳያል። ለዚህ ነው የስዎን “ልባዊ ምክር” አንድም ቅንነቱን፣ ብሎም ተፈጻሚነቱን የምጠራጠረው። ቅቤ ላይወጣው አጓት መናጥ!

ዶ/ር ዓቢይ መተኪያ የሌለውና፣ እስዎ ያኔ ያነበንቡለት እንደነበረው አለቃዎ "ብቸኛና ቆራጥ መሪ" ናቸው ማለቴ ሳይሆን፣ ዛሬ ይህንን መቶ ቦታ የተከፋፈለ አስተሳሰብና በቡድናዊ ዓላማ የተመረዘን የፖሊቲካ እንሳሳ ፍላጎት የሚያሟላ ትንግርታዊ ፎርሙላ ያለው ግለሰብ ያለ ስላልመሰለኝ ነው። ሕገ መንግሥቱም እንደዚሁ እኛ ስላልወደድነው ብቻ የሚፈርስ አይደለም። ሕገ መንግሥቱን ለመሻር ወይም ለማሻሻል የሚቻለው ራሱ ሕገ መንግሥቱ ባስቀመጠው መስፈርት ብቻ ሲሆን፣ ዛሬ ይህንን በተግባር ሊተረጉም የሚችለው ብቸኛ አካል ደግሞ በሕዝብ ያልተመረጠው ፓርላማ ነው። ዶ/ር ዓቢይም ሃሳቡን ከማቅረብ ያለፈ ሕገ መንግሥቱን ለመሻርም ሆነ ለማሻሻል መብት የለውም። ችግሩ ግን፣ ባንድ በኩል፣ የሕገ መንግሥቱ አርቃቂዎችና የዛሬዎቹ የፓርላማ አባላት ሕዝቡን ስለማይወክሉ ሕገ መንግሥቱ "ሕዝባዊ" አይደለም እያልን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሕጋዊ ያልሆነ ፓርላማ ወይም ደግሞ በሕዝብ ያልተመረጠው ዶ/ር ዓቢይ፣ ሕገ መንግሥቱን ያፍርስ ወይም ያሻሽል ማለቱ ትንሽ ግራ የገባ ነገር ነው። ለማንኛውም፣ ሕገ መንግሥቶቻችን እስከዛሬ ሕዝባዊ ሆነው ስለማያውቁ፣ ምናልባት የሚቀጥለው ምርጫ ዲሞክራሲያዊ ሆኖ፣ እውነተኛ የሕዝብ ተወካዮች ተመርጠው ፓርላማ ሲገቡ፣ ሕገ መንግሥቱን የማሻሻል ወይም አፍርሶ አዲስ የማወጅ ዕድል ይኖራቸዋልና ዛሬ እምብዛም ባያሳስብዎት ጥሩ ነው ባይ ነኝ።

ሻለቃዬ! ወደድንም ጠላንም፣ ተቀበልነውም አለተቀበልነው፣ የዶ/ር ዓቢይ መንግሥት በዚች ባንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጦችን አስመዝግቧል። አዎ! ገና ብዙ ብዙ መሠራት ያለባቸውና መሞላት ያለባቸው ቀዳዳዎች አሉ። ይህ ደግሞ በሂደት እንጂ እኛ ስለፈለግነው ወይም ስለተመኘነው ብቻ በተዓምር ባጭር ጊዜ ሊቀረፍ የሚችል ጉዳይ አይደለም። ይዋል ይደር እንጂ ጊዜያቸውን ጠብቀው መፈታታቸው ግን አይቀርም። እንኳን ዛሬ የዶ/ር ዓቢይ መንግሥት አንጻራዊ ዲሞክራሲ ለማስፈን እየሞከረ ባለበት ጊዜ ይቅርና እስዎም በአመራር ደረጃ በተካፈሉበት የደርግ ዘመን እንኳ አገራችን ከዚህ በጣም ከከፋ ቀውስ ውስጥ ነው በሂደት አገግማ የወጣችው። ምክንያቱም የኢትዮጵያን ሕዝቦች ከሚለያዩአቸው ይልቅ የሚያዛምዳቸው ይበልጣልና! ዛሬም ቢሆን እንደስዎ ያሉ ጨለምተኞችና ሟርተኞች ጣልቃ እየገባችሁ አታዳክሟት እንጂ እናት አገራችን አፈር ልሳም ቢሆን ተነስታ በግሯ እንደምትቆም ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለኝም። አቢቹም እንዳለው "ኢትዮጵያ ከስታ ይሆናል እንጂ አትሰበርም"! ዝም ብለን ጉድለትን ብቻ ጎላ አድርጎ ከማቅረብ ሙላትንም በትንሹ እንኳ ብናወድስ ብሩኅ ነገን የማየት ዕድላችንም የሰፋ ይሆናል። ሁሌም መርሳት የሌለብን ነገር ግን፣ ዛሬ የዶ/ር ዓቢይ ቡድን እየተጓዘበት ያለው ጎዳና ከዚህ በፊት በዘመናዊው የኢትዮጵያ የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ታሪክ ውስጥ ተሞክሮ የማይታወቅ መሆኑን ነው።

ላገራችንና ሕዝባችን የምንመኘው ለውጥ በኛ ትውልድ ዘመን ደርሶ ላናይ እንችላለን። ያም እየታወቀ ግን፣ የሚቀጥለው ትውልድ እኛ ዛሬ ከምንኖርባት የተሻለች ኢትዮጵያ እንዲኖር ከልባችን የምንመኝ ከሆነ ጠንካራ የማዕዘን ድንጋዮችን ዛሬ ተባብረን መትከል አለብን። ትናንት "ጣናን ኬኛ" እና "የኦሮሞ ደም የኛም ደም ነው" የሚሉትን መሳጭ አባባሎችን ከቆለፍንባቸው ሳጥኖች አውጥተን እንደገና ማዜም መጀመር አለብን! ብዝሃነታችን ዉበታችን፣ ልዩነታችን ደግሞ ጥንካሬያችን መሆኑን እየተገንዘብን፣ ሕዝባችንን በጥቃቅን ጉዳዮች ከመከፋፈል እንቆጠብና ለታላቁ ራዕይ መተግበር በጋራ እንሥራ! የጥገናዊ ለውጥ ጉዞ በጣም ረጅም ነው። እኛ ተጓዦቹ ደግሞ ጉዞው አድካሚ መሆኑን ከወድሁ ተረድተን፣ አስፈላጊውን ስንቅና ትጥቅ በጥንቃቄና ብስለት በተሞላበት ዘዴ ካላዘጋጀን፣ መሃል መንገድ ላይ መዳከምና ተስፋ መቁረጥ ሊመጣና ካለምነው ግብ ሊያሰናክለን ይችላል። ዋናውና ሁሌም መገንዘብ ያለብን ጉዳይ ግን፣ ይህንን ረጅም ጉዞ በአሸናፊነት የምንወጣው አብረን ተደጋግፈን ከተጓዝን ብቻ ነው።

በመጨረሻ ለማለት የምፈልገው ግን ሻለቃዬ! በያኔ በሥልጣን ዘመንዎ የትና ምን እንደነበሩና ስለማውቅ ብስዎ ምክር ውስጥ ቅንነትን ማየት በጣም ያዳግተኛል። በዚህ ደግሞ ሊወቅሱኝ አይገባም። ስለፈጸሟቸው ወይም ተባባሪ ስለሆኑባቸው የሰው ልጆች ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እርገፍ አርገን ትተን እስዎንም እስከነመኖርዎ ረስተንዎት ነበር። የመንግሥትዎን የጅምላ ግድያና ማሰቃየትን አስመልክቶ አንድም ቀን አንድም ቦታ ላይ የተቃውሞ ድምጽዎን ያላሰሙና፣ ሥልጣንዎን ተጥቅመው ድርጊቱን ለማስቆም ወይም በመኮነን አንዳች ዓረፍተ ነገር ያልተነፈሱ ባላሥልጣን፣ ዛሬ ዓይንዎን በጨው ታጥበው፣ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ምክር ለመስጠት ብቅ ማለትዎ አልዋጥ ብሎኝ ነው። በግድ ምክር መስጠት አለብኝ ካሉ ደግሞ፣ ካለፈው የሥልጣን ዘመንዎ ተሞክሮ፣ ጥሩ ጥሩውን ለይተው እንድንጠቀምባቸው፣ መጥፎ መጥፎውን ደግሞ ለይተው "እያዋጣችሁምና በዚያ መንገድ አትሂዱ" ብሎ በቀና መምከር ነው እንጂ፣ ያ ያራመዱትን መጥፎ ፖሊሲ እንኳ ሳይቀር "ጥሩ ነውና ግፉበት" እያሉ ለመምከር ሲሞክሩ ማየቱ ዕውነትም እኛ ኢትዮጵያውያን ጭንቅላታችን ምንኛ በክፋት እንደተሞላና ከለምደነው አሠራር ውጪ ሌላ ለመልመድ ምንኛ እንደሚከብደን ያሳያል። አሮጌ ልምድ በቀላሉ አይለቅም (old habits die hard) ይላሉ ፈረንጆች! ከጅብ ጅማት የተሠራ ክራር ቅኝቱ ሁሌም እንብላው እንብላው ብቻ ነው ያሉት አበው፣ እውነትም በተሞክሮአቸው ያዩት ነገር ቢኖር ነው!! በቸር ይግጠመን።

ጀኔቫ፣ አፕሪል 15 ቀን 2019 ዓ/ም

wakwoya2016@gmail.com